# አዘርባጃን በኢትዮጵያውያን ወጣቶች አይን

ለበርካታ አመታት የአዘርባጃን መንግሥት “ስለአዘርባጃን የማውቀው ምንድን ነው?” በሚል ርዕስ በመጣጥፍ ውድድር መልክ ልዩ ፕሮጀክት ሲተገብር ቆይቷል፡፡ የውድድሩ አላማ በአዘርባጃን ወጣቶችና በወዳጅ አገሮች መካከል መካከል የውጭ ግንኙነትን ለማስፋፋት፣ ሰዎች ከአገሪቱ የበለጸገ የባህልና የታሪክ ቅርስ፣ ዘመናዊ ልማትና የተሻለ መሠረተ ልማት ራሳቸውን በግል የሚያስተዋውቁበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እንዲሁም የአዘርባጃን ጓደኞች በወዳጅ አገሮች ከሚገኙ አቻዎቻቸው ጋር የሚኖራቸውን ጓደኝነት ለማስፋፋት ነው፡፡


ሁለት ከወዳጅ አገር ኢትዮጵያ የመጡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሆኑ ሁለት ተሳታፊዎች የውድድሩ አሸናፊ ሆነው በአዘርባጃን ጉብኝት ለማድረግ ተጋብዘው ነበር፡፡ የውድድሩ አሸናፊዎች ስለጉዟቸው ያላቸው አስተያየት ከታች ቀርቧል፡፡

**<u>እየሩሳሌም ተክሉ አርአያ፣- የአዘርባጃን ቆይታዬ</u>**

ኦገስት 25 ቀን ከሌሊቱ 9፡00 ሰአት ገደማ ባኩ ደረስን፡፡ እዚያ በየቦታው መብራት ነበር፤ ከተማዋ ደማቅና የሞቀ













እንቅስቃሴ የሚታይባት ነበረች፣ ሆኖም በእርግጥ በመደበኛ ሁኔታ ባኩን ለማግኘት እስከሚቀጥለው ቀን መጠበቅ ነበረብን፡፡ በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ከተማዋ በቀን ብርሃንም ውብ መሆኗን መረዳት ችያለሁ፡፡ መንገዶቿ ንጹህ ናቸው፣ በዘመናዊና አሮጌ በዱሮ ኪነሕንጻ መካከል የሚታይ ፍጹማዊ ሚዛን አለ፡፡ አንዳንዶቹ ሕንጻዎች ታሪካዊ ይመስላሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ መጤ ይመስላሉ፣ አንዳንድ ሕንጻዎች ጸጥታ የሰፈነባቸው የሚያምሩ ነበሩ፤ ሌሎቹ ደግሞ ትኩረት የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ከአንድ ሳይት ወደሌላው በአውቶቡስ ስንጓዝ በመንገዱ ግራና ቀኝ ያሉትን ድንቅ ሕንጻዎች በመስኮት አተኩሬ ማየት ነበር የምወደው፡፡

እዚያ በነበረኝ ቆይታ  ከሌሎች 45 አገሮች ከመጡ አሸናፊዎች ጋር በየቀኑ አዳዲስ ሳይቶችን ጎብኝተናል፣ እያንዳንዱ ሳይት የራሱ ታሪክ ነበረው፡፡ የብሄራዊ የመጋረጃ ሙዚየሙን አዳራሾች በእግር ተንቀሳቅሼ ጎብኝቻለሁ፣ ቀደም ሲል ካየኋቸው  በጣም ከሚያምሩ ሙዚየሞች አንዱ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ በጣም አስደሳች ከሆኑት ታሪካዊ ምስሎች አንዱን የያዘውን የሃይደር አሊየቭ ማዕከልንም ጎብኝቻለሁ፡፡ በመንገዶቹ ወደላይና ወደታች በእግር ተንቀሳቅሼ የ3 ሺ አመት እድሜ ያላቸውን የላሂጅና የሼኪ ከተሞች አሮጌ መንደሮችም ጎብኝቻለሁ፡፡ ከዚያ በኋላ አዘርባጃን በባኩ ውስጥ የሚገኙ በርካታ አስደናቂ የቱሪስት ሳይቶች ያሏት አገር መሆኗን ብቻ ሳይሆን ከዋና ከተማዋ ውጭ ውብ መስህብ ያላት መሆኑንም በቀላሉ መረዳት ችያለሁ፡፡ አዘርበጃንን ለመጎብኘት ካገኘሁት እድል በተጨማሪም ይህ ጉዞ ከሌሎች 9 አገሮች ከመጡ ተማሪዎች መካከል አብረን ሳይት በማየትና አብረን በመመገብ ከጓደኛዬ ከራኬብ ጋር ለመገናኘት እድል ፈጥሮልኛል፣ በመንገዳችን አንዳንድ ጓደኞች ማፍራት ችለናል፡፡ ከሰዎች ጋር መገናኘትና ተሞክሮ መለዋወጥ መቻል በአዘርባጃን መንግሥት የተሰጠን ሌላ አስደሳች እድል ነበር፡፡

ከዚያም በአዘርባጃን በነበረኝ ቆይታ ከሁሉ የወደድኩት







የመራራ ፍራፍሬና የወይን ፌስቲቫል ነበር:: ፌስቲቫሉ ግልጽ፣ ውብና ደማቅ ነበር:: መብላት ከፈለግክ ምግብ ነበረ፣ መደነስ ከፈለግህ የሚያስደንስ ሙዚቃ ነበረ:: ፌስቲቫሉ በባህላዊ የአዛሪ ሙዚቃና ዳንስ ነበር የተከፈተው:: በእንደዚህ አይነት ውብ ዝግጅት በመሳተፌ ነበር የተደሰትኩት፣ ሁነቱን ፎቶ ለማንሳት በቂ ጊዜ ማግኘት አልቻልኩም:: ያለምንም ጥርጥር ፌስቲቫሉ በእርግጥም በቅርቡ አንድ ቀን በድጋሚ ልሳተፍበት ያሰብኩበት አይነት ነው:: በየሄድንበት ቦታ ሰዎች በፈገግታ ነበር ሰላምታ የሚሰጡን፣"ከየት ናችሁ?" የሚል ጥያቄም ነበር የሚጠይቁን:: የአዘርባጃን ሕዝብ ጥሩና የማወቅ ጉጉት ያለው ሕዝብ ነው:: በእግርና በታክሲ በምንቀሳቀስበት ጊዜ ከአንዳንድ የአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ለመነጋገር እድል አግኝቼ ነበር፣ ብዙዎቹ ኢትዮጵያ የምትባል አገር የት እንደምትገኝ የማያውቁ ቢሆንም ከሞላ ጎደል ሁሉም ንግግር ወደአገራችን እንኳን ደህና መጣችሁ በሚል አነጋገር ነበር የሚጠናቀቀው:: ይህ ተቀባይነት ያገኘሁ መሆኑ እንዲሰማኝ አድርጎኛል::

ሌላው ያጋጠመኝ አስደሳች ነገር መንግሥት የሚሠራው ከወጣቶች ጋር የሚሠራው ሥራ ነበር:: ይህ ኢትዮጵያን ጨምሮ በአለም ለሌሎች አገሮችም ጥሩ መማሪያ ሊሆን የሚችል ተሞክሮ ይመስለኛል:: ከምክትል ሚኒስትሩ ጋር ካደረግነው ስብሰባ የአዘርባጃን መንግሥት የሚሠራው ለወጣቱ ሳይሆን ከወጣቱ ጋር መሆኑን በቀላሉ መረዳት ችያለሁ:: መንግሥት በወጣቱ ላይ ተጽእኖ ሊያስከትሉ በሚችሉ ፖሊሲዎች ዙሪያ ከወጣቱ ጋር አንድ ላይ ነው የሚሠራው:: ይህ በኢትዮጵያ እውን ሆኖ ማየት የምፈልገው ነገር ነው፣ ምክንያቱም ሁላችንም እንደምናውቀው ወጣቱ የነገ አገር ተረካቢ በመሆኑ ነው::

ለማጠቃለል በአዘርባጃን የነበረኝ ቆይታ በቀላሉ አስደሳች ነበር:: እድሉን በማግኘቴ እድለኛ ነኝ ብዬ አስባለሁ:: አዘርባጃን የሚነገር ታሪክና የምታጋራው ቴክኖሎጂ ያላት አገር ነች:: በቆይታችን ለማንኛውም የሚያሳስበን ጉዳይ ምላሽ ለመስጠት፣ ጉዟችን በትክክል እንደሆነው በአስደሳችና አዝናኝ ተሞክሮ የተሞላ እንዲሆን ለማድረግ የሚሞክሩ ታላላቅ አስተባባሪዎች ነበሩን:: ያረፍንበት ሆቴል በካስፒያን ባሕር አቅራቢያ የሚገኝ ነበር፣ በቡለቫርዱ ወደላይና ወደታች ለመንቀሳቀስ የሚያስችል ውብ ነበር:: ባኩ ውብና የሚስቡ ሕንጻዎችና ሃውልቶች አሏት፣ ሌሎች ብዙ ኢትዮጵያውያን ከተማዋን መጎብኘት እንደሚችሉ ተስፋ አደርጋለሁ:: ጉዞውን የበለጠ አስደሳች ለማድረግ አስተዋጽኦ የነበራቸው ሌሎች 45 ተማሪዎችም ነበሩ:: ይህን እድል በማግኘቴ በጣም አመሰግናለሁ::

**ራኬብ መስፍን ተሰፋዬ፡ - የእሳት ምድር የተደረገ ጉብኝት**

አዘርበጃን ከጎበኘኋቸው ሁሉ በጣም አስደሳች ሥፍራ ነች:: ለመጎብኘት እድል ባገኘሁባቸው በሁሉም ታሪካዊ ቦታዎችና የንፋስ ከተማ በሚል የተለመደ መጠሪያ በምትታወቀው (በባኩ) ባየሁት ሁሉ ተደምሜያለሁ፤ በጣም ውብና አስደሳች ነበር፣ በጥንት ረጅም ልቦለድ ድርሰት በብዙዎቹ ደራሲዎች ከተገለጹት አይነት የጥንት ከተሞች አንዷን ትመስላለች:: ባሁኑ ጊዜ ይህን የሚመስሉ ሌሎች ብዙ ቦታዎች ያሉ አይመስለኝም:: ለባኩ ዘመናዊ ነገር ግን ጥንታዊ ገጽታ ያላበሷትን አሮጌና ዘመናዊ ሕንጻዎች አንድ ላይ ቆመው ለማየት በጣም የሚያነቃቃ ነገር ነበር:: ባኩ በመንገዶቿ በእግር የሚንቀሳቀሱ ሰዎችን ልብና ነፍስ የሚያረጋጋ ሰላማዊ የመንፈስ እርካታ ሰፍኖ የሚገኝባት ከተማ ነች:: የአዘርባጃን የባህልና የልማድ ስሜት በጣም ጠንካራ ነው:: የአዘርባጃን ሕዝብ በመዘመንና በለውጥ ሂደት ሁሉ የራሱን ማንነት ጠብቆ የኖረ ህዝብ መሆኑን መታዘብ ችያለሁ::

ጉዞው እስካሁን ካጋጠሙኝ ምርጥ ተሞክሮዎች አንዱ ነበር፣ ከጎበኘኋቸው ከሁሉም ሥፍራዎች፣ ለእያንዳንዱ ቦታ ተዘጋጅተው ከተነገሩ ታሪኮችና ከአዘርባጃን ሕዝብ ልዩ የጎሣ ማንነት፣እንዲሁም አገራቸውን እንዴት በራሳቸው ማሻሻልና መገንባት እንደቻሉ ብዙ ተምሬያለሁ:: ተቆጣጣሪዎቻችን ትልቅ ፕሮግራም ነበር ያዘጋጁት፣ በአዘርባጃን በነበረን የ10 ቀን ቆይታ ማየት የነበረብንን ሁሉንም ነገር ሊያሳዩን ችለዋል:: የእስማኤል ከተማን፣ የላሂ መንደርን፣ የሼኪ ከተማን የጋባላ ከተማን የመሳሰሉ ጥንታዊ ነገር ግን የአዘርባጃን ሕዝብን ባህልና ልማድ አጉልተው የሚያንጸባርቁ ከተሞችን



ጎብኝተናል፡፡ በጥንት ጊዜያት የተሰሩ  አስካሁን ድረስ ቆመው የሚገኙ ውብ መኖሪያ ቤቶች ማየት ችለናል፡፡ አንድም ዋና ጉዳት ሳይደርስባቸው በጥሩ ሁኔታ የተጠበቁ ቤቶች ማየት አስደናቂ ነበር፡፡ ለማጣበቂያ እንቁላልና የኖራ ድንጋይ ብቻ በመጠቀም በአዛርባጃኒዎች የተሠሩትን እነዚህን ጥንታዊ ቤቶች ማየት አስደናቂ ነበር፣ በእኛ ኢትዮጵያውያን ፋሲለደስን የመሳሰሉ ጥንታዊ ሕንጻዎቻችን የተሠሩበትን መንገድ አስታውሶኛል፡፡

በግል ከጎበኘናቸው ከሁለቱም ሥፍራዎች ጉልህ ግምት የሚሰጠው የዛን ሳራቪ ቤተ መንግሥትና የሃይደር አሊዬቭ ማዕከል ነው፤ የሼኪ ካንስ ቤተመንግሥትም ከጎበኘኋቸው ቤተመንግሥቶች ሁሉንም የሚያስንቅ አስደናቂ እንደነበር በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ፡፡ የካን ቤተሰብ የበጋ መኖሪያ ቤትም በጣም ውብና ታሪካዊ ነው፡፡  የቤተመንግሥቱን ሁሉንም የግድግዳ ሥዕሎችና ንድፎችና ምን ማለት እንደሆኑ ገለጻ ያደረገልን ጥሩ አስጎብኚ ነበረን፡፡ ለዚህ ቤተመንግሥት አሁን ባለበት ሁኔታ እድሳት ያደረጉለት ሁለት አርክቴክቶች እንዴት አድርገው ሥራቸውን እንደሰሩ በአስጎብኚያችን ገለጻ ተደርጎልናል፤ ቤተ መንግሥቱ ሁለት ፎቅ አሉት፣ የመጀመሪያው ክፍል የንጉሱና የእንግዶቻቸው ሲሆን የዚህ ክፍል በር ባልተለመደ ሁኔታ አጭር ነው፤ ምክንያቱም ንጉሱን ለመጎብኘት የሚመጡ እንግዶች ወደ ክፍሉ ከመግባታቸው በፊት ለቤተሰቡ ያላቸውን አክብሮት ለማሳየት እንዲያጎነብሱ ለማድረግ ታስቦ የተሠራ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ክፍል ንጉሱ



ስምምነት በሚያደርጉበት ጊዜ ከውጭ የሚያንዣብቡ ሌሎች እንግዶች እንዳያዩ ለመከካከል በግድግዳው አንድ ጎን ፋውንቴን አለው፡፡ ክፍሉ ግድግዳውና ጣራው በቅብ ሥዕሎች ያጌጠ፣ መስኮቱ በሚያምር የክሪስታል መስታወት ፍሬም የተሠራ፣ ሲከፈት ከፊት የአትክልት ቦታ የሚያሳይ፣ የሚቀጥለው ክፍል አነስተኛ ቢሮ ያለው እዚያ የሚሠራ ማንኛውም ሰው ሃሳቤ ሳይበተን በሥራው ላይ ብቻ አተኩሮ እንዲሠራ ለማድረግ ታስቦ ግድግዳው ምንም የቅብ ሥዕል ጌጥ ወይም የቀለም የሌለው ነው፤ ከሁሉ የሚያስደንቀው ጎብኚዎች በሚመጡበት ጊዜ እተጌዋ የበለጠ የግል ነጻነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ታስቦ በቢሮውና ከላይ ባለው





የእተጌዋ መኖሪያ መካከል አንድ ሜትር ባዶ ቦታ የተተወ መሆኑ ነው፡፡ ያየነው ሌላው ክፍል የበለጠ የቤተሰብ ክፍል የሚመስል የንድፎችና የሥዕሎች ቅብ ያለው ነው፡፡ የተለያዩ የቅብ ሥዕሎች አይተናል፣ ሆኖም ከሁሉም የወደድኩት በአሳ አናት ላይ ቆሞ ያየሁት የአንበሳ ምስል ነው፡፡ በዚህ ሥዕል የአንበሳው ግማሽ ሰውነት ዘውድ የደፋ ጭራው በአንበሳው ጭንቅላት ላይ እሳት የሚተፋ ደራጎን የሚያሳይ ነው፡፡ ከሁሉ የሚያስደንቀው ይህ የሚወክለው ከሁሉም ጠንካራው ንጉሥ እንኳን በአስቸጋሪ ጊዜያት ሊያልፍ የሚችልና ሕይወት ምንጊዜም በጣም የተረጋጋ ሳይሆን ቁልቁለት የበዛበት ሊሆን እንደሚችል ነገር ግን ከንጉሱ ወይም ከመሪው ጎን ጎበዝ ሴት እስካለች ድረስ አለምን ማሸነፍና ካንዣበበበት ችግር መውጣት እንደሚችል ነው፡፡ ጭራው እንደ ደራጎን የአንድ ሰው ጠላት ሌላ ሰው ወይም የውጭው አለም ሳይሆን የራሱ አስተሳሰብ መሆኑን ያሳያል፣ ይህም እኛ የሰው ልጆች መጥፎ ሃሳብ ስናስብ በሕይወታችን ማሳካት የምንፈልገውን ነገር እንዳይሳካ አእምሮአችን ገድቦ እንደሚይይዘን ያሳያል፡፡

ዲዛይኑ በዛሃ ሃዲድ የተሠራው የሃይደር አሊዬቭ ማዕከል ቀደም ሲል አይቼው በማላውቀው የሚያምር ኩርባ የተሠራ ነው፣ የጋለሪ አዳራሽና ሙዚየም ይዟል፡፡ ሙዚየሙ ታሪካዊ እሴት ያለበት ሲሆን በወቅቱ ስለነበረው ታላቁ መሪና ስለ ሥራ ውጤቶቹ የተማርንበት ነበር፡፡ በተጨማሪም በማዕከሉ



ውስጥ ያየናቸው የተለያዩ ሃውልቶችና ሥዕሎች ሕንጻው በአይነቱ የመጀመሪያው ልዩ እንዲሆን ያደረጉ ነበሩ፡፡

ባጠቃላይ በአዘርባጃን የነበረኝ ቆይታ በጣም ድንቅና የሕይወት ዘመን ተሞክሮ ያገኘሁበት ነበር፡፡ በማዕከሉ ሁሉንም ቦታዎችና የአዘርበጃንን ሕዝብ ባህላዊ እንቅስቃሴ የሚያሳዩ ትዕይንቶች ማየት በመቻሌ በጣም ደስተኛ ነኝ፡፡ ከኢትዮጵያ ምግቦች በጣም የተለዩ ባህላዊ ምግቦችን የሚመለከት ተሞክሮ በማግኘቴ በጣም ደስ ብሎኛል፣ በተጨማሪም ባየሁት የወይን እርሻ በወይን ፌስቲቫል ተሳታፊ በመሆኔ ደስ ብሎኛል፡፡ በጣም አስደሳች ተሞክሮ ነበር ማለት እችላለሁ፡፡ ይህችን አስደናቂ አገር ለማየት እድል በማግኘቴ ይህን ጉዞ ያመቻቸውን የአዘርባጃን ኤምባሲንና ሁሉንም ሠራተኞቹን በጣም ማመስገን እወዳለሁ፡፡

